የዴንቨር
የሕዝብ
ት/ቤቶች

የዕድልን ዓለም ያግኙ™

የዴንቨር እቅድ ለ2020

# ሁሉም ልጅ ስኬታማ ይሆናል









# መግቢያ

እያንዳንዱ ልጅ በት/ቤት ያን የመጀመሪያ  እርምጃቸውን ቢራቢሮዎች ... እና ችሎታ፣ እምቅ አቅም እና ህልሞች ይዘው ይጀምሩታል። ይህ የት/ቤት መጀመሪያ ቀን በትምህርት የውጭውን ዓለም በር የሚከፍቱበት ይሆናል።  ያም ማለት ***እያንዳንዱ*** ልጅ፣ የትም ቢኖሩ፣ ወላጆቻቸው የትኛውንም ያህል ገቢ ቢኖራቸውም፣ የትኛውም የችሎታ ደረጃ ውስጥ ቢሆኑም፣ ወይም የቆዳቸው ቀለም የትኛውም  እያንዳንዱ ልጅ ከፍተኛ ጥራት ያለው ት/ቤት ይገባዋል/ታል፣ እናም ሁላችንም ወሳኝ ሚና አለን፦ ቤተሰቦች በልጆቻቸው ትምህርት በመሳተፍ፣ አስተማሪዎች ከፍ-ያሉ ግቦችን በመያዝ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት እና በመከታተል፣ እና ሁሉም በንቃት በመሳተፍ እና በልጆቻችን እና በከተማችን የወደፊት ዕድል ላይ ኢንቨስት ማድረግ።

ለልጆቻችን የዕድል ዓለምን በር መክፈት ብቻ በቂ አይሆንም። በዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ *ሁሉም ልጅ ስኬታማ ይሆን ዘንድ የጋራ ራዕያችን ነው።* እንዲማሩበት የመረጡት ት/ቤት ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ / ልዩነት ሳይፈጥር ተማሪዎቻችን እንክብካቤ የሚደረግላችው መሆኑን፣ የሚፈትናቸው ትምህርት የሚቀርብላቸው መሆኑን፣ የሚበረታቱና ድጋፍ የሚደረግላቸው መሆኑን እና በኮሌጅ፣ በሥራ እና በሕይወት ስኬታማ መሆን የሚችሉ መሆናቸውን እርግጠኞች መሆን ያስፈልገናል። ከዚያ ጊዜያዊ እና መጀመሪያ ከሆነው ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት ጀምሮ መጨረሻና ልበ-ሙሉነት የሚሰማበት የምረቃ ቀን ድረስ፣ ዕንቡጦቹን ለመንከባከብ እና እምቅ ችሎታቸውን ለማውጣት ነው እዚህ ያለነው።

የዴንቨር የ2020 እቅድ ዲስትሪክቱ የት ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት እና ሰዎችን፣ ጊዜን እና ገንዘብን እንዴት በሚገባ መመደብ/መጠቀም እንዳለበት ጨምሮ ለዲስትሪክቱ ውሳኔ-አሰጣጥ ሂደት አቅጣጫ ያሳያል። እቅዱ ጎዳናችን ወደ 'ሁሉም ልጅ ስኬታማ ይሆናል' ይመራልናል።

# ያሳካነው

አስተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የማኅበረሰብ አባላት ወደ *ሁሉም ልጅ ስኬታማ ይሆናል* ራይ ጉዞ ጀምረውታል። የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች  (DPS) የዴንቨር እቅድን መጀምሪያ በ2006 (እ.ኤ.አ.) አዘጋጀ፤ በ2010ም አሻሻለው። ውጤቶቹ ተስፋ ሰጭ ናቸው። ባለፉት ስድስት ዓመታት፣ DPS  በሚደንቅ ሁኔታ የቅድመ-መደበኛ እና የመዋዕለ-ህፃናት ትምህርት ዕድሎችን አስፋፍቷል፣ የምዝገባ መጨመርን አሳይቷል፤ በክልሉ (ስቴቱ) ውስጥ ካሉት ዋና ዋና ዲስትሪክቶች መካከል ከፍተኛውን የተማሪ መሻሻል ድረጃን አሳይቷል፣ ለመመረቅ የሚበቁ ተማሪዎችን ምጣኔ በ23 በመቶው ነጥቦች ሲጨምር የሚያቋርጡ ተማሪዎች ምጣኔን ደግሞ በግማሽ ቀንሷል።

ራዕያችን ግልጽ እድገታችንም እርግጥ ቢሆንም ፊትለፊታችን መጓዝ ያለብን መንገድ ረዥም ነው። DPS  በሀገሪቱ ውስጥ በፍጥነት እያደገ ያለ የከተማ ዲስትሪክት እንዲሆን ለአደረጉት ለአስተማሪዎቻችን ቁርጠኝነት እና ጠንክሮ መስራት አድናቆት እና ምስጋና እናቀርባለን። ይህ በዚህ እንዳለ፣ ሰፊው የውጤት ክፍተት አልተዘጋም፣ እንዲሁም ሁሉም ልጅ ውጤታማ እየሆነ አይደለም።

DPS አዳዲስ ፈጠራዎችን እና ለውጦችን ለማስቀጠል ካለፉት በርካታ ዓመታት ልምድ እና ጥንካሬ በመነሳት ውጤታማ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው ለውጦች ላይ እና አዳዲስ ስልቶችን በመቀየስ ላይ ያተኩራል። በ2014 (እ.ኤ.አ.) አጋማሽ ውስጥ ወደ 3,000 የሚጠጉ ጠቃሚ ግብረመልስ የሰጡን ባለድርሻ አካላት፦ ተማሪዎችን፣ ወላጆችና ቤተሰቦችን፣ መምህራን፣ የት/ቤት አመራሮችን፣ የማህበረሰብ አጋሮችን እና ሌሎች የት/ቤት ዲስትሪክት ሠራተኞችን አነጋግረናል። በዚህ ግብዓት ላይ በመመርኮዝ፣ ጥቂት የሆኑ ወሳኝ ግቦችን እና ቁልፍ የስልቶች ቅደም-ተከተል አውጥተናል። ልጆቻችን በደንብ ዝግጁ፣ ውጤታማ፣ እና ማኅበራዊ ተሳትፎ የሚያደርጉ አዋቂዎች ለመሆን በሚገሰግሱበት ጎዳና ማንኛውም ጠቀሜታ/ድጋፍ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ DPS የጥራት ጣራውን ከፍ በማድረግ ላይ ነው።

# እምነታችን

በDPS ለምንሰራው ሁሉም ሥራችን የጋራ ዐበይት እሴቶቻችን እና እምነቶቻችን እንደ ጽንዑ መሠረት ያገለግሉናል፤ የባሕላችን ምንነት ናቸው።

የጋራ ዐበይት እሴቶቻችን ሁሉም ልጆች ስኬታማ ይሆናሉ የሚለውን ራዕያችን ለማሳካት በምንሰራው ሥራ አንድ ያደርጉናል፤ እንዲሁም እንዴት መሥራት እንዳለብን አቅጣጫ ያሳዩናል። ኦገስት 2012 ከዲስትሪክቱ በመላ በተውጣጡ ከ1,000 በላይ በሆኑ ሰዎች የተዘጋጁት እነዚህ እሴቶች የምንጋራውን ባሕላችን ቅርጽ ያስይዙታል፤ እንዲሁም ግቦቻችን ለማሳካት እንድንችል የውሳኔዎቻችን መመሪያ ይሆናሉ።

## የDPS የጋራ ዐበይት እሴቶች

**ቅድሚያ ተማሪዎች፡-**
ከማንኛውም ከምንሰራው ነገር ሁሉ በፊት የልጆቻችን ፍላጎቶች እናስቀድማለን።

**ታማኝነት፡ -**
እውነቱን እንናገራለን፤ እንዲሁም ቃሎቻችን እንጠብቃለን።

**እኩልነት/ፍትሃዊነት፡ -**
ብዝሃነታችን እናከብራለን እና ለሁሉም ልጆቻችን የስኬት እንቅፋቶችን ለማስወገድ እንዲችሉ እና ይበልጥ ፍትሀዊ የሆነ መጪ ጊዜን ለማውረስ አስፈላጊ መረጃዎችን/አቅርቦቶችን እና ድጋፎችን እናቀርባለን።

**ትብብር፡ -**
ግቦቻችንን ለመምታት አብረን እንደ አንድ ቡድን እናስባለን፤ እንሰራለን፤ እና እንፈጥራለን።

**ተጠያቂነት፡ -**
ለግል እና ለጋራ ሥራዎቻችን ኃላፊነት እንወስዳለን፤ በስኬታችን ይበልጥ እንበረታታለን፤ ከስህተቶቻችን እንማራለን።

**ደስታ፡ -**
በሥራችን መደሰትን እናከብራለን፤ እንዲሁም በተማሪዎቻችን ውስጥ ለመማር ያላቸው ደስታ እና ፍቅር ሙሉ ዘመናቸውን እንዲሰርፅ እናግዛቸዋለን።



## ራዕያችን፡- ሁሉም ልጅ ስኬታማ ይሆናል

### በእያንዳንዱ መንደር ምርጥ ምርጥ ት/ቤቶች



## የተማሪ ሥነ-ሕባዊ ዳታ (ዲሞግራፊክስ)










## አጠቃላይ የት/ቤቶች ብዛት፡- 183




## ዐበይት እምነቶቻችን

ዐበይት እምነቶቻችን በጋራ ዐበይት እሴቶቻችን ላይ የተመሰረቱ እና ጥረቶቻችንና ግብዓቶቻችን አቅጣጫ/ቅደም-ተከተል ለማስያዝ እንዲሁም ስኬትን እንዴት እንደምንለካው ለመወሰን የሚያስችሉን ናቸው። የሚከተሉትንም እናረጋግጣለን፡-

- **እያንዳንዱ ልጅ ተሰጥዖ እና እምቅ ችሎታ አለው።**
  ለእያንዳንዱ ልጅ ጠንካራ፣ ሁለ-ገብ እና ከባህል ጋር የተስማማ ትምህርት መሰጠት እና ድጋፍ ማድረግ የእኛ ፋንታ ነው።
- **ልዩነቶቻችን አስደናቂ ስጦታዎቻችን ሲሆኑ እኩልነት ደግሞ የተልዕኳችን ዕምብርት ነው።**
  የእያንዳንዱን ልጅ ልዩ ማንነት እና እምቅ አቅም ሊያቅፍ የሚችል ባሕል ለመገንባት ቁርጠኞች ነን።
- **የውጤት ልዩነቶችን (ክፍተቶች) ሊያመጡ የሚችሉ የአቅርቦት (የዕድል) ልዩነቶችን/ክፍተቶችን ለማስወገድ እንችላለን፤ እናስወግዳለንም።**
  በት/ቤት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ ከስኬት ሊያሰናክሉ የሚችሉ እንቅፋቶች ማስወገድ፣ ተጠያቂነት ላይ ማተኮር፣ እና ግብዓቶችን የሚያስፈልገውን ተማሪ አስቀድመን መምረጥ/ማለም ፣ ድጋፍ እና ተጽኖ ማድረግ አለብን።
- **በሚሰራ እና አዳዲስ ፈጠራን በሚያቅፍ ጉዳይ ላይ ኢንቬስ በማድረግ እድገታችን በሚደንቅ ሁኔታ ማፋጠን አለብን።**
  የ21ኛው መ/ክ ዘመንን የሚመጥን ደረጃ ያለው ትምህርት በመስጠት፣ ተማሪዎችቻችን ለኮሌጅ፣ ለሥራ እና ለሕይወት ዝግጁ በመሆን ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲመረቁ እናበረታታቸዋለን።
- **እያንዳንዱ ቤተሰብ ከፍተኛ፥ጥራት ያለው በአኅራባቹ ት/ቤቶች ሊመርጥ እና ሊያገኝ ይገባዋል።**
  በዲስትሪክቱ በሞላ እጅግ በጣም ጥሩ ት/ቤቶችን ለማቅረብ ቁርጠኞች ነን።
- **ልጆቻችን ሁላችንም - አስተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን፣ የማኅበረሰ አጋሮችን እና የሥራ ባልደረባዎችን ይፈልጉናል - እናም ሁላችንም በጋራ የDPS ቡድን ነን።**
  በግልጽነት፣ በለውጥ-አምጭ /proactive/ ንግግር እና በመሻሻል ስልቶችን ዙሪያ ወላጆችን ማኅልበት እና ከእነሱ ጋር መተባበር አለብን።

# ቀጣይ መንገዳችን

መድረኩን ለመላው የዴንቨር ማኅበረሰብ መክፈታችን (እ.ኤ.አ.) በ2020 ከሌሎች አራት ደጋፊ ግቦች ጋር አንድ አጠቃላይ ግብ በጋራ ለማውጣት አስችሎናል። በእነዚህ አምስት ግቦች ለተማሪዎቻችን ስኬት ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች ላይ እናተኩራለን። እነዚህን ግቦች ማሳካት ከቻልን ሌሎች አዎንታዊ ውጤቶች ይከተላሉ።

## ግብ 1 — ምርጥ ምርጥ ት/ቤቶች በእያንዳንዱ መንደር

ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ምርጫዎች ሲኖሯቸው ለመሻሻል (የተሻለውን ለማግኘት) ይጥራሉ። በዲስትሪክቱ በሞላ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ ሁሉም ልጅ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ለማግኘት እድል ይኖረው ዘንድ DPS በየመንደሩ የሚገኙትን ት/ቤቶች ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል።

በ2020 80% የሚሆኑ የDPS ተማሪዎች በዲስትሪክቱ የት/ቤት አፈጻጸም ምዘና ማዕቀፍ መሠረት ከፍተኛ አፈጻጸም ባላቸው ት/ቤቶች የሚማሩ ይሆናል።



**ከፍተኛ አፈጻጸም ያለው ት/ቤት የሚከታተሉ ተማሪዎች**

አሁን **61%** → 2020 **80%**

## ግብ 2 — በት/ቤት ውስጥ ለስኬት መሠረት

በቅድመ-መደበኛ የልጆች ትምህርት ዝግጁነት ትኩረት ማደረግ ለአንድ ተማሪ የአጠቃላይ የትምህርታዊ/አካዳሚያዊ ተሞክሮ ጠቃሚ መሠረት ይጥላል። 3ኛ ክፍል ላይ በደንብ የሚያነቡ እና የሚጽፉ ተማሪዎች 10ኛ ክፍል ላይ በማንበብ፣ በመፃፍ እና በሂሳብ የክፍል ደረጃቸው ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ብቃት ይኖራቸዋል። ስለዚህ DPS ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት እስከ 3ኛ ክፍል ላሉት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ላልሆነ ልጆች ጠንካራ ትምህርት እና ድጋፍ በማድረግ በዝግጁነታቸው ላይ ትኩረት ያደርጋል።

በ2020, 80% የDPS ሁሉም ሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች በማንበብ እና በመፃፍ፣ *Lectura* እና *Escritura* በክፍል ደረጃቸው ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ብቃት ይኖራቸዋል።*

መነሻ ወደ የጋራ ዐበይት / Common Core/ ሽግግር በሚደረግ ጊዜ ሊለወጥ ይችል ይሆናል፣ እናም በ2015-16 የግብ ማስተካከያ ያስፈልግ ይሆናል።



**3ኛ ክፍል የማንበብ እና የመጻፍ ብቃት**

አሁን **60%** → 2020 **80%**

**የምረቃ ምጣኔ**

| አሁን | | 2020 |
|---|---|---|
| 68% | → | 90% |

**ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁ ሆነው የሚመረቁ ተማሪዎች**

| አሁን | | 2020 |
|---|---|---|
| 1100 | → | 2200 |

**አፍሪካ-አሜሪካዊ እና ላቲኖ የምረቃ ምጣኔ**

| አሁን | | 2020 |
|---|---|---|
| 64% | → | 89% |

**አፍሪካ-አሜሪካዊ እና ላቲኖ የ3ኛ ክፍል ማንበብ እና መፃፍ ብቃት**

| አሁን | | 2020 |
|---|---|---|
| 50% | → | 75% |

## ግብ 3 ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁ

የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን እና ቀድሞውኑ ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎችን ጨምሮ ሁሉንም ተማሪዎች የራሳቸውን ዕጣ ፋንታ እንዲያበጁ በማነሳሳት፣ በመፈተን እና በማጎልበት የመጭውን ወጣት ትውልድ ልበ-ሙሉነት፣ ብቁነት እና ጤናማ የሥራ ሥነ-ምግባር እንቀርፃለን። DPS ውጤታማ የሆኑ ለኮሌጅ-እና-ሥራ-ዝግጁ ምሩቃን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል።

በ2020 ከዘጠንኛ ክፍል ጀምሮ በDPS ለሚማሩ ተማሪዎች የአራት-አመት የምረቃ ምጣኔ ወደ 90% ያድጋል።

በ2020 ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁ ሆነው የሚመረቁ ተማሪዎች ቁጥርን እየጨመረ በመጣው የስቴት ደረጃ./ስታንዳርድ ልኬት መሠረት በእጥፍ እንጨምራለን።

## ግብ 4 ድጋፍ ለምሉዕ ልጅ

DPS የአንድን ልጅ ሙሉ ስብዕናን ለማሳደግ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ቁርጠኛ ነው። የት/ቤቶቻችን አካባቢዎች ተማሪዎች ስሜቶቻቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን ለመከተል፣ የአካላዊ ጤንነታቸውን ለመጠበቅ፣ እንዲሁም ስሜቶችን መቆጣጠር፣ አዎንታዊ ግንኙነቶችን መመሥረት እና ማስቀጠልና ኃላፊነት የተሞላባቸው ውሴኔዎችን መወሰንን ጨምሮ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጓቸውን የማኅበራዊ/ስሜታዊ ክህሎቶችን ማጠናከር ያስችላሉ።

በ2015 የDPS የሥራ ባልደረቦችን፣ የማኅበረሰብ አጋሮችን እና ለDPS ተማሪዎች አገልግሎት የሚያቀርቡ የከተማ ኤጀንሲዎችን ያካተተ ግብረ-ሃይል ይህን ግብ የመለካት እና ለውጦቹን የማጥናት ዕቅድ ለትምህርት ቦርዱ ያቀርባል።

## ግብ 5 የዕድል ልዩነትን/ክፍተትን መዝጋት

ሁሉም ተማሪዎቻችን የሚችሉትን ከፍተኛ የውጤት ደረጃዎችን እንዲያስመዘግቡ ለሚያስችሏቸው ትምህርታዊ ዕድሎችን ማግኘት ይገባቸዋል። ይህ ማለት በነጭ ተማሪዎቻችን እና በአፍሪካ-አሜሪካዊያን እና በላቲኖ ተማሪዎቻችን ለረጅም ጊዜ የዘለቀ ልዩነት/ክፍተት እንዳለ እያወቅን ለሁሉም ተማሪዎች የውጤት ደረጃ ጣራውን ከፍ ማድረግ ማለት ነው። በዘር ጉዳይ ላይ ማተኮር እና ድህነት ምክንያት ባልሆነበት ሁኔታ እንኳ የተለያየ ቀለም ባላቸው ተማሪዎቻችን መካከል የውጤት ልዩነት/ክፍተት መኖሩ ልክ እንዳልሆነ እናምናለን። በእነዚህ ምክንያቶችም በዕድሎች/በአቅርቦቶች ልዩነት/ክፍተት ላይ የሚያተኩር ግብ ማስቀመጣችንም ውሳኝ እንደሆነ ይሰማናል።

በ2020 የአፍሪካ-አሜሪካዊ እና ላቲኖ የመመረቅ ምጣኔ በ25 በመቶው ነጥብ ከፍ ይላል።
የ3ኛ ክፍል አፍሪካ-አሜሪካዊ እና ላቲኖ ተማሪዎች የማንበብ እና የመፃፍ ችሎታ በ25 በመቶው ይጨምራል።*

*መነሻ ነጥቡ ወደ የጋራ ዐበይት /Common Core/ ሽግግር በሚደረግ ጊዜ ሊለወጥ ይችል ይሆናል፣ እናም በ2015-16 የግብ ማስተካከያ ያስፈልግ ይሆናል።

# እንዴት መድረስ እንችላለን

ራዕይ ዕውን የሚሆነው በድርጊት ብቻ ነው። የስልቶቻችን የትኩረት ቅደም-ተከተል DPS ግብዓቶቹን ምን ላይ ማሰባሰብ እንዳለበት አቅጣጫ ይሰጣሉ፤ እንዲሁም ግቦቻችን ለማሳካት የሚያስፈልግ መሠረት ይጥላሉ። አምስቱ የተቀዳሚ ትኩረት መስኮች የሚከተሉት ናቸው:-

## አመራር:-

- ➜ በDPS በሞላ በጠንካራ እሴቶች ላይ የሚመራ አመራርን መሳብ፣ ማልማት እና ማቆየት።
- ➜ በት/ቤቶች ውስጥ የመምህራን አመራርን በማልማትና በማበረታታት የተከፋፈለ/የተዋረድ አመራርን ማጎልበት።
- ➜ ከውስጥ ኮትኩቶ ማሳደግን፣ የት/ቤት መሪ ዝግጅት ፕሮግራሞችን እና ተነባጠረ ማለማመድ /mentorship/ ጨምሮ ለአመራር ጠንካራ ተተኪ ማዘጋጀት።
- ➜ የት/ቤት አመራሮች ለተማሪዎቻቸው ስኬት እና የት/ቤታቸው ማኅበረሰቦች ልዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተዘጋጁ፣ ድጋፍ የሚደገፉ እና ተጠያቂነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ።

## ማስተማር:-

- ➜ የክፍል ደረጃ ይዘት ልክን በሚገባ በመተግበር እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ምርጥ የማስተማር ስልት ተሞክሮዎችን በመጠቀም የክፍል ውስጥ ትምህርት ጥራትን እና ጥንካሬን ይኸ ነው በሚባል ሁኔታ መጨመር።
- ➜ ግብረ መልሶችን እና የስልጠና ቋጠሮዎችን
- ➜ ለእያንዳንዱ የDPS ት/ቤት ውጤታማ መምህራንን ከፍተኛ፡ፍላጎቶች ባላቸው ት/ቤቶቻችን እንዲያስተምሩ ለመቅጠር፣ ለማሳደግ እና ለማቆየት ጥረታችን ማጠናከር።
- ➜ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ለባሕል ተስማሚ/ኃላፊነት ያለው ትምህርት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ስልቶችን ሥራዬ ብሎ መንደፍ።

## ተለዋዋጭነት /Flexibility/:-

- ➜ የሀብት/ግብዓቶች አጠቃቀምን ጨምሮ እንደየሁኔታው ሊቀየር በሚችል /flexible/ የት/ቤት ውሳኔ አሰጣጥ ት/ቤቶችን ማጎልበት።
- ➜ በአዳዲስ የት/ቤት ስልቶች ተመዝጋቢ ቁጥርን በመጨመር ጥረቶች እና በጠንካራ የተጠያቂነት ሥርዓቶች አሁን ላሉት ት/ቤቶች በተለይ ድጋፎችን በማድረግ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ት/ቤቶችን ለሁሉም ማኅበረሰቦች ምርጫ ማስፋት።
- ➜ ለት/ቤቶች የግላዊ-ትምህርት የማግኛ ከባቢን ጨምሮ የተማሪዎቻቸውን ትምህርታዊ/አካዳሚያዊ እና ማኅበራዊ/ስሜታዊ ፍላጎቶችን በጥራት የሚያሟሉበት ከባቢ ለመፍጠር እና ለማዘጋጀት የሚያስችሏቸው እድሎች መስጠት።

## ቀደም ብለው ኢንቨስት ያድርጉ:-

- ➜ ህፃናት ተማሪዎቻችን ለቀጣይ የክፍል ደረጃዎች ስኬት ለማዘጋጀት ለታችኞቹ (ቅደመ-መደበኛ እስከ 3ኛ) ክፍሎች ግብዓቶች/አቅርቦቶችን ቅድሚያ እናቀርባለን።
- ➜ ለትምህርታዊ/አካዳሚያዊ ስኬት መሠረትን ለመጣል ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ድጋፎችን እና አገልግሎቶችን ህፃናት ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች አቅርቦትን ማስፋፋት።

## ባሕል:-

- ➜ የጋራ ዓበይት እሴቶቻችን መኖር፣ ማክበር እና ተጠያቂነትንም መውሰድ።
- ➜ በሁሉም ት/ቤቶቻችን ቤተሰብን ኣን ማኅበረሰብን ሊያቅፍ የሚቸል አዎንታዊ እና አቅምን የሚያጎልብት ባህልን መገንባት።
- ➜ በDPS ድጋፍ ክፍሎች እና በDPS አጋሮች መካከል ት/ቤቶችን የማገልገል ባሕል ማዳበር።








## ጥሪ ለእርምጃ/ለድርጊት

ሁሉም ልጅ ከፍተኛ ግቦች ባሉበት ድባብ ውስጥ መሆን ይገባዋል። በዚህ ዕቅድ ውስጥ የተገለጹትን ግቦች ለማሳካት ባለፉት ቅርብ ዓመታት ውስጥ በተማርነው እና ባካበትነው ላይ መመሥረት እና ከመምህራንና ት/ቤት አመራር ጀምሮ እስከ ተማሪዎቻችን፣ ቤተሰቦች እና የማኅበረሰብ አጋሮቻችን ድረስ በሰዎች ላይ ያለንን ትኩረት ከፍ ማድረግ አለብን። ሁሉም ዋጋ ይሰጠዋል፤ እናም ሁሉም ወሳኝ ሚና መጫወት አለበት።

- እኛ በDPS ያለን በዚህ ዕቅድ ውስጥ ለተቀመጡት ግቦች እና ስልቶች/ስትራቴጂዎች ተጠያቂዎች ነን።
- መምህራን፣ የት/ቤት አመራሮች፣ የሥራ ባልደረቦች ሁላችሁንም ተማሪዎቻችን ወደ ከፍተኛ ግቦች እንድታደርሱልን እና እነዚያን ከፍተኛ ደረጃዎች/ስታንዳርዶች ደግሞ በእናንተ በራሳችሁ ባሕርይ ውስጥ እንደ አርአያ እንድትጠቅሙባቸው (ሞዴል እንድታደርጓቸው) እንጠይቃችኋለን።
- ወላጆች እና ቤተሰቦችን ደግሞ በቤታችሁ ውስጥ የልጆችን ደረጃ (የሚጠበቅባቸውን የጥራት ደረጃ) ጣሪያ ከፍ እንድታደርጉ እና ልጆቻቸው ለስኬት የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንድታደርጓልቸው እንጠይቃለን።
- የማኅበረሰብ አጋሮችንም የበለጠ ጊዜያችሁን እና እውቀታችሁን በቁርጠኝነት እንድታበረክቱ እንጠይቃችዋለን።

በጋራ ህልማችን እውን እናደርጋለን - ሁሉም ልጅ ስኬታማ ይሆናል!




**የዴንቨር እቅድ ቅርጽ ያገኘው በብዙዎች አስተዋጽዖ ነው፤ ልዩ ምስጋና ለ፦**

**ቦርድ**
ሃፒ ሃይንስ /Happy Haynes
አርቱሮ ጂምኔዝ/Arturo Jimenez
ማይክ ጆሃንሰን/Mike Johnson
ባርባራ ኦብሬን/Barbara O'Brien
ሮዝሜሪ ሮዲሪግ
/Rosemary Rodriguez
አን ሮዌ/Anne Rowe
ላንድሪ ቴይለር/Landri Taylor

**አንጋፋ የአመራር ቡድን**
ቶም ቦስበርግ
/Tom Boasberg
ክሪስቲን ኮሎን
/Kristin Colon
ሱዛን ኮርዶቫ
/Susana Cordova
ኢቫን ዱራን/van Duran
ቬሮኒካ ፊጎሊ
/Veronica Figoli
ዲቢ ኸርቲ/Debbie Hearty
ዊሊ ሊ-አሽሌ
/Will Lee-Ashley
አሌክስ ማርቲቴኔ/Alex Martinez
ግሬታ ማርቲኒ/Greta Martinez
ሻይን ስፓልተን/Shayne Spalten
ዴቪድ ሱፐስ/David Suppes
ሚካኤል ቫውግኸን/Michael Vaughn
አሊሳ ዋይትሄድ-በስት
/Alyssa Whitehead-Bust

**የዴንቨር እቅድ አማካሪ ኮሚቴ**
ሮንዳ ቤን/Ronda Belen
ብራንዶን ብሊው/Brandon Blew
ካትሪና ማን ቦይኪን
/Katrina Mann Boykin
ፍራንክ ኮይን/Frank Coyne
ኒኮላስ ዳውኪንስ
/Nickolas Dawkins
ካረን ፎክስ ኢትዌል
/Karen Fox Elwell
ክሪስ ጊቦንስ/Chris Gibbons
ጆዜት ማርቲኔ ግሪፊን
/Jozette Martinez Griffin
ብሩክ ጆንሰን-ብራውን
/Brooke Johnson-Brown
ኪም ክኑስ-ዶላን
/Kim Knous-Dolan
ጀኒፈር ሞሪሰን
/Jennifer Morrison
ሊንድሴይ ኔል/Lindsay Neil
ኢቮን ፖራስ/vonne Porras
ኒታ ሬስኬ/Nita Reske
ዛክ ሮይ/Zach Rowe
ጁንታ ስቲቨንሰን/Juanita Stevenson
Aአዳም ቮሌክ/dam Volek
ቻክ ዋርድ/Chuck Ward

**ባልደረባ/ሠራተኞች**
ኒኮል ብራንስ ኬሪ
/Nikole Bruns Carey
ደስቲን ክሬስ/Dustin Kress
ጀኒፈር ስተርን
/Jennifer Stern



Denver Public Schools Emily Griffith Campus 1860 Lincoln St. Denver, CO 80203 720-423-3200 info@dpsk12.org www.dpsk12.org